Public Health
Seattle & King County

# የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ(አርኤስቪ)

**ውድ ወላጅ እና አሳዳጊ፣**

**ይህ የእውነታ ወረቀት የቀረበልዎት ምክንያት:**

☐ **እርስዎ ወይም ልጅዎ ለየመተንፈሻ አካላት ቫይረስ(አርኤስቪ)ተጋልጠው ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው።**

☐ **ለመረጃ አገልግሎት ብቻ።**

---

## ስለ የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ(አርኤስቪ) አጠቃላይ መረጃ

### የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ(አርኤስቪ) ምንድን ነው?

- በትናንሽ ህጻናት ላይ ብዙውን ጊዜ መለስተኛ እና ጉንፋን መሰል ምልክቶችን የሚያመጣ የመተንፈሻ አካላት ቫይረስ ነው።
- በተለይ ለጨቅላ ህጻናት እና ለአዋቂዎች ከባድ ሊሆን ይችላል።
- የተለመደ እና ሁሉም ልጆች እስከ 2 ዓመታቸው ይያዛሉ።
- በክረምት ወይም በጸደይ መጀመሪያ ወቅት የተለመደ ነው።
- ከ1 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት እንደ ብሮንካይተስ እና የሳምባ ምች የመሳሰሉ ዝቅተኛ የመተንፈሻ አካላት (ሳንባዎች) ኢንፌክሽኖች ተደጋጋሚ መንስኤ ነው።

### ማን ሊይዘው ይችላል?

- ማንኛውም ግለሰብ ቀደም ብሎ በጉንፋን ቢያዝም እንኳን እንደገና በጉንፋን ሊያዝ ይችላል።
- አንዳንድ የህብረሰብ ክፍሎች በጣም ሊታመሙ ወይም ለከፍተኛ የህክምና ችግሮች ሊጋለጡ ይችላሉ፣ ቡድኖቹ እነዚህም በታች ያሉትን ያጠቃልላል:
  - ጨቅላ ህጻናት እና ትንንሽ ልጆች
  - ከ50 ዓመት በላይ የሆኑ ግለሰቦች
  - እርጉዝ ሴቶች
  - የተዳከመ በሽታን የመከላከል አቅም ያላቸው ወይንም ሥር የሰደደ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች
- **በበሽታው ምክንያት ለከፍተኛ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦች (ከላይ ያለውን ይመልከቱ) ለ አርኤስቪ ተጋልጫለሁ ብለው ካሰቡ የጤና እንክብካቤ አቅራቢቻቸውን ማነጋገር አለባቸው።**

### ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

- ትኩሳት (የአሜሪካ የሕፃናት ሕክምና አካዳሚ ትኩሳትን 100.4ºF [38ºC] ወይም ከዚያ በላይ የሙቀት መጠን አድርጎ ይገልፃል።
- የአፍንጫ ፍሳሽ
- ማስነጠስ
- ማሳል
- የምግብ ፍላጎት ማጣት
- በተለይ በትናንሽ ጨቅላ ህጻናት (ከ 6 ወር በታች) እና አርኤስቪ ያለባቸው ጨቅላ ህጻናት ላይ ተጨማሪ ምልክቶች መታየት አለባቸው።
  - ዝቅተኛ የእንቅስቃሴ ደረጃ
  - መነጫነጭ

- የምግብ ፍላጎት ማጣት
- በፍጥነት መተንፈስ ወይም የመተንፈስ ችግር (የሚንቀጠቀጡ የአፍንጫ ቀዳዳዎች፣ ማጉረምረም፣ ጩኸት ጨምሮ)

- አብዛኛዎቹ ምልክቶች ከ8 እስከ 15 ቀናት ውስጥ ይጠፋሉ።

**እንዴት ነው የሚሰራጨው?**

- ቫይረሱ በሳል፣ በማስነጠስ፣ በለሐጭ እና ከአፍንጫ በሚወጡ ፈሳሾች ውስጥ ይገኛል።
- አርኤስቪ የያዘው ሰው ሲያስል ወይም ሲያስነጥስ አጠገብ ያለው ሰው የወጡትን ጠብታዎች ከተነፈሰ ቫይረሱ ሊሰራጭ ይችላል።
- እንዲሁም ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች ሊሰራጭ ይችላል:
  - አርኤስቪ ቫይረስ ያለበትን ነገር ከነኩ በኋላ አይንን፣ አፍንጫን ወይንም አፍን በመንካት።
  - አርኤስቪ ከያዘው ግለሰብ ጋር የምንጠቀምባቸውን ዕቃዎች ወይም ኩባያዎች መጋራት።
- አርኤስቪ ለብዙ ሰአታት በነገሮች ላይ ሊኖር ይችላል።
- አንድ ሰው ምልክቱ መታየት ካቆመ በኋላም ቢሆን ለሳምንታት የአርኤስቪን ቫይረስ ሊያሰራጭ ይችላል::

---

## ልጄ የመተንፈሻ አካላት ሲንሰሻል ቫይረስ (RSV) እንዳለበት እንዴት አውቃለሁ?

- የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ቫይረሱን ለማግኘት ከአፍንጫ ወይም ከጉሮሮ ላይ ፈሳሽ ጠርጎ መውሰድ ይችላል።
- የአርኤስቪ ኢንፌክሽንን ለመለየት የደም ምርመራዎችም ሊደረጉ ይችላሉ።

**ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉህ ወይም ልጅህ አር ኤስ ቪ ይኖረዋል ብለህ የምታምን ከሆነ ለጤና አገልግሎት ሰጪህ ንገረው ። ይህ የእውነታ ወረቀት አጠቃላይ መረጃን ብቻ ነው የሚያቀርበው።**

---

## ልጄ አርኤስቪ ቢኖርበትስ?

**ልጅዎ አርኤስቪ ከያዘው ወዲያውኑ ለልጅዎ ሐኪም ወይም ቅድመ-ትምህርት ቤት ማእከል ያሳውቁ።**

**ምን አይነት ህክምናዎች አሉ?**

- ለ አርኤስቪ የተለየ መድሃኒት የለም፣ ነገር ግን ልጅዎን የበለጠ እንዲመችው ለማድረግ አንዳንድ ምልክቶችን ማከም ይችላሉ። ስለ ሕክምና አማራጮች ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ህጻናት ልጆን ምቾት እንዲሰማቸው ያድርጉ፣ እረፍት እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው፣ የውሀ እጥረትን ወይም ድርቀትን ለመከላከል ብዙ ፈሳሽ መጠጣታቸውን ያረጋግጡ እና ቶሎ ቶሎ ሁኔታቸውን ይከታተሉ።
- 3 ወር ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ጨቅላ ህጻናት 100.4ºF (38ºC) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት ካለባቸው በጤና እንክብካቤ አቅራቢያቸው መታየት አለባቸው።
- ስለ ልጅዎ የበሽታው ምልክቶች የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ከልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይነጋገሩ። **ልጅዎ የውሀ እጥረት ወይም የድርቀት ምልክቶች እያሳየ ከሆነ (ጥቂት እርጥብ ዳይፐር፣ ከወትሮው ያነሰ ጥቂት ሽንት፣ ከወትሮው የበለጠ ድካም፣ መፍዘዝ፣ ደረቅ ምላስ ወይም ከንፈር፣ ሲያለቅስ ትንሽ እንባ)፣ በጣም በፈጣን እየተነፈሰ ከሆነ፣ የመተንፈስ ችግር ካጋጠመው ወይም ከባድ ራስ ምታት ካለበት ወዲያውኑ በጤና እንክብካቤ አቅራቢ መታየት አለበት።**

Public Health
Seattle & King County

**አርኤስቪ እንዳይሰራጭ እንዴት መርዳት እችላለሁ?**

- ሲታመሙ ቤት ይቆዩ።
- በተለይም ካስነጠሱ፣ ከሳሉ ወይም አፍንጫዎን ከጠራርጉ በኋላ፤ እጅን በሳሙና እና በሞቀ ውሃ አዘውትረው ይታጠቡ፣
- በሚያስሉበት ወይም በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፍንጫዎን እና አፍዎን ይሸፍኑ።
- አይኖችዎን፣ አፍንጫዎን እና አፍዎን ከመንካት ይቆጠቡ።
- ኩባያዎችን፣ የምግብ ዕቃዎችን፣ ምግብ እና መጠጦችን አርኤስቪ ካለው ከማንኛውም ሰው ጋር ከመጋራት ይቆጠቡ።
- ህጻናት አሻንጉሊቶችን እና ሌሎች ነገሮችን በሳሙና እና በውሃ አፋቸው ውስጥ በደንብ ያጽዱ።
- የቤት ውስጥ ቦታዎችን በፀረ፡ተህዋሲያን ያጽዱ::

---

## ልጄ ከልጆች እንክብካቤ መስጫ ተቋማቱ ቀርቶ እቤት መቆየት አለበት?

**አይ እቤት መቅረት የለበትም።  የመተንፈሻ አካላት ሲንስሻል ቫይረስ (RSV) በሽታ የተጋለጡ ልጆች ወይም ተመርምረው በሽታው እንደያዛቸው የወቁ ልጆች ከዚህ በታች የተጠቀሱት ነገሮች ካልሆኑ በስተቀር ወደ ሕፃናት እንክብካቤ መስጫ መሄዳቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ:**

- ከሌሎች የአርኤስቪ ምልክቶች ጋር የተያያዘ ትኩሳት (የሙቀት መጠኑ 100.4$^{0}$F [38ºC] ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ)
- በተቋማቱ ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ በቂ የጤና ስሜት ካልተሰማው (ለምሳሌ: ከወትሮው የተለየ ድካም፣ የመነጫነጭ ወይም የመበሳጨት ስሜት ካለው፣ ወይም ከተለመደው በላይ እያለቀሰ ከሆነ)።

**እባክዎ የልጅዎትን የእንክብካቤ ፕሮግራም የበሽታ ፖሊሲ ይከተሉ።**

---

**የመረጃ ማጣቀሻዎች/ምንጮች:**


American Academy of Pediatrics

- *Caring for our Children, Chapter 3 Health Promotion and Protection, 3.6 Management of Illness, 3.6.1 Inclusion/Exclusion Due to Illness*
- *Caring for our Children, Chapter 7 Infectious Diseases, 7.3 Respiratory Tract Infections, 7.3.8 Respiratory Syncytial Virus (RSV)*
- *Managing Infectious Diseases in Child Care and Schools, 5th Edition. pages 147-148*

Centers for Diseases Control & Prevention

- *Respiratory Syncytial Virus Infection (RSV). https://www.cdc.gov/rsv/*

Child Care Health Program – Public Health Seattle & King County

- *https://kingcounty.gov/depts/health/child-teen-health/child-care-health/disease-prevention.aspx*